# የእድሜ ማራዘሚያ መድሐኒት (Antiretroviral Treatment)

በብሮነር ጎንሳልቭስ

በህክምና ታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ ከሆኑት ግኝቶች ውስጥ አንዱ የእድሜ ማራዘሚያ ወይም አንቲሬትሮቫይራል ቴራፒ (antiretroviral therapy) ህክምና ነው። ይህ የህክምና ዘዴ ለHIV/AIDS ዋና ማስታገሻ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ግን ፈውስ እንዳልሆነ ተረጋግጧል።

ህክምናው የተለያዩ እይነቶች አሉት። እነዚህ አይነቶች የሚወሰኑት ቫይረሱ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ በመገንዘብ ነው። አይነቶቹ በአራት ሊከፈሉ ይችላሉ። እነሱመም ኒውክሊዮሳይድ/ኒውክሊዮታይድ ረቨርስ ትራንስክሪፐቴዝ ኢንሂቢተርስ (Nucleoside/Nucleotide Reverse Transcriptase Inhibitors) ነንኒውክሊዮሳይድ ረቨርስ ትራንስክረፐቴዝ ኢንሂቢተርስ (Non-Nucleoside Reverse Transcriptase Inhibitors) ፕሮቲዬዝ ኢንሂቢተርስ (Protease Inhibitors) እና ፊውዥን ወይም ኤንትሪ ኢንሂቢተርሰ (Fusion or Entry Inhibitors) በመባል ይታወቃሉ። ኒውክሊዮሳይድ የተባለው አይነት በመጀመሪያ የተፈበረከው ሲሆን የተሰራውም እ.አ.አ. በ80ዎቹ መጨረሻ ላይ ነው። ግን ይህ መድሐኒት ጠቃሚነቱ የታየው እ.አ.አ በ90ዎቹ መሀል ላይ እንደሆነ ታውቋል። ይህም ሊሆን የቻለው ሀኪሞች ይህን መድሃኒት ከሌሎች ጋር ደርበው በማዘዛቸው ነው። ይህ የመድሐኒቶች ቅልቅል ኮክቴል ተብሎ የተሰየመ ሲሆን ጠቃሚነቱም የጎላው ቫይረሱ እራሱን እንደሚቀይርና አንድ መድሃኒት ለብቻው ሊከላከለው ባለመቻሉ ነው። በአሁኑ ጊዜ ከሃያ በላይ መድሃኒቶች ገበያ ላይ ሲኖሩ ከአንድ ቫይረስ ተከላካይ ንጥረነገር ብቻ እና ከብዙ ንጥረነገሮች የተሰሩ ይገኙበታል።

በእድሜ ማራዘሚያ መድሐኒት ለመታከም ሲታሰብ የተለያዩ ምርመራዎችን ማድረግ ያስፈልጋል። ለምሳሌ የቫይረሱን ስርጭት (viral load) እና ሲዲ ፎር ካውንት (CD4+ count) መታወቅ ይኖርበታል። እነዚህ ምርመራዎች የእድሜ ማራዘሚያ መድሐኒቱ ወዲያውኑ ወይም ዘግይቶ መጀመር እንዳለበት ይጠቁማሉ። ከቫይረሱ ስርጭትና ከመድሐኒቱ ጋር የሚመጡ ተግጓዳኝ ህመሞች መሐል የትኛው ለበሽተኛው አደገኛ እንደሆነ መገንዘብም ያስፈልጋል። ብዙውን ጊዜ የሚታሰበው ማንኛውም የHIV ቫይረስ ተሸካሚ ወዲያውኑ መድሐኒቱን መጠቀም እንዳለበት ነው። ነገርግን ይህ ትክክል አይደለም። አስፈላጊው ምርመራ ተደርጎ ለዛ በሽተኛ መድሐኒቱ በእርግጥ ጠቃሚ እንደሆነ መረጋገጥ አለበት። ሌላው የተሳሳተ አስተሳሰብ ደግሞ መድሐኒቱን የሚጠቀሙ ሰዎች ለሞት የተቃረቡ ብቻ ናቸው የሚለው ነው። ይህ እውነት አይደለም ምክኒያቱም በሙሉ ጤና ያሉ የቫይረሱ ተሸካሚዎች መድሐኒቱን መውሰድ ስለሚችሉ ነው። አንዳንድ የቫይረሱ ተጠቂዎች ደግሞ ይህ የእድሜ ማራዘሚያ መድሐኒትን መውሰድ ከጀመሩ የስራ ገበታቸውን መልቀቅ እንዳለባቸውና በየጊዜው ወደ ሆስፒታል መመላለስ እንደሚኖርባቸው ያስባሉ። ይህ የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው ምክኒያቱም መድሐኒቱ በክኒን መልክ ስለሚሰጥ ታካሚው እንደ ማንኛውም ሰው መስራትና መኖር ይችላል።

መቼ ነው ከአንድ መድሐኒት ወደሌላ መለወጥ ያለበት? መድሐኒቱን ከሚጠቀሙ ታካሚዎች መሃል ግማሽ ያህሉ መድሐኒቱን በጀመሩ በአንድ አመት ውስጥ ለውጥ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ለዚህም 3 የተለያዩ ምክኒያቶች ይጠቀሳሉ። እነዚህም የበሽታዎች መከሰት (የተቅማጥ በሽታ፤ የደም ማነስና የሃሞት ቀረጢት) መድሐኒቱ መስራት ማቆም እና ከጊዜ በኋላ የሚከሰት የጤና መታወክ ይገኙበታል።

ምንም እንኳን የእድሜ ማራዘሚያ መድሐኒቶች (antiretroviral drugs (ART)) ለብዙ የቫይረሱ ተጠቂዎች ተስፋም ቢሰጡ ዋጋቸው ለታዳጊ ሀገሮች በጣም ከፍተኛ ነው። UNAIDS የተባለ ድርጅት እንዳስታወቀው ከሆነ እ.አ.አ በ2006 39.5 ሚሊዮን ሰዎቸ በቫይረሱ

ተጠቅቷዋል እና ከነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ በታዳጊ ሃገራት የሚኖሩ ናቸው። በነዚህ ሀገራት ከሚኖሩት ተጠቂዎች በጣም ጥቂቶቹ ናቸው የአድሜ ማራዘሚያ መድሃኒቶችን መጠቀም የሚችሉት። ሞትን ለመከላከል እነዚህ መድሃኒቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው። የመድሃኒቶቹ እጥረት የቫይረሱን ተሸካሚዎችን ህይወት በእጅጉ ያሳጥራል።